| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "አስተያየት ። " |
| ርእስ ፤ | • "መንግሥት ፡ ወይስ ፡ መንግሥታዊ ፡ ያልኾነ ፡ ድርጅት?" |
| ደራሲ ፤ | የ "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ አንባብያን ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2012-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ካንባብያን ፡ የደረሱ ፡ አስተያየቶች ። ) |

## አስተያየት
## Opinion | رأي

# "መንግሥት" ፡ ወይስ ፡ "መንግሥታዊ ፡ ያልኾነ ፡ ድርጅት"?

*[...] እስከሚገባኝ ፡ ድረስ ፥ መንግሥት ፡ ማለት ፡ በሕዝብ ፡ ውክልና ፡ ሀገርን ፡ በሥልጣን ፡ ለማስተዳደር ፡ የተቋቋመ ፡ አካል ፡ ነው ። ታዲያ ፡ 50% ፡ ባጀቱ ፡ በውጭ ፡ መንግሥታት ፡ የሚሸፈንለት ፡ "መንግሥት" ፥ "ፖሊሲ" ፡ ብሎ ፡ የሚይዛቸው ፡ ሥራዎች ፡ የውጭ ፡ መንግሥታትና ፡ ተቋማት ፡ የወሰኑለትና ፡ ወጪውንም ፡ የሚችሉለት ፡ ተኾነ ፥ ምኑን ፡ "መንግሥት" ፡ ኾነ? ከኹለት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ለ 2010 ፡ ዓ.ም. ፡ የብሪታንያ ፡ መንግሥት ፡ 70 ፡ ሚልዮን ፡ ፓውንድ ፡ ለኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ አገዛዝ ፡ በመስጠት ፥ "በሚመጡት ፡ አራት ፡ ዓመታት ፡ 4 ፡ ሚልዮን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ከመወለድ ፡ ያስወግዳል" ፡ ለተባለው ፡ ለወሊድ ፡ መቈጣጠሪያ ፡ ዕቅድ ፡ እንዲያውለው ፡ ተደርጓል ። ይህ ፡ ዕቅድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ወይ ፡ የተወካዮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የፈቀደው ፡ ስለ ፡ መኾኑ ፡ የሰማኹት ፡ ነገር ፡ ስላልነበረ ፥ የ GTP1 ፡ እና ፡ የ GTP2 ፡ ሰነዶችን ፡ አገላብጬ ፡ አየኹ ፥ እነዚህም ፡ ላይ ፡ ስለወሊድ ፡ መቈጣጠሪያ ፡ "ፖሊሲ" ፡ ምንም ፡ ዝርዝር ፡ ነገር ፡ ዐጣኹ ።*

*ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ፈቃድ ፡ ውጪ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ነገሮች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ኹኔታዎች ፡ ስለሚታዩ ፥ በውነቱ ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚገዛው ፡ አገዛዝ ፡ "መንግሥት" ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ "መንግሥታዊ ፡ ያልኾነ ፡ ድርጅት"? ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡ ተገደድኹ ። [...]*

*በላይ ፥ ከዐዲስ ፡ አበባ ።*


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።